


# እናት ኢትዮጵያ አደይ ኤርትራ — ከአንተነህ መርዕድ

መሳይ መኮንንና ፋሲል የኔዓለም ወደ ኤርትራ ያደረጉት ጉዞ የብዙ ኢትዮጵያውያንን እንዲሁም የኤርትራውያን ወንድምና እህቶች ቀልብ መሳቡ እሙን ነው። በተለይም የፕሬዝደንት ኢሳያስ አፈወርቂ ቃለ መጠይቅ በብዙ መልኩ አስደምሞናል። እድላችን የተቆራኘነውና መነጋገሩና መብሰልሰሉ የሚገባ በመሆኑ ያለፍንበትን ሁሉ በትዝታ እንድፈትሽና አሁን የደረስንበትን እንዳይ ምክንያት ሆኖኛል። ነገሮችን ውስብስብና አጠቃላይ ከሆነ መልኩ ይልቅ ተጨባጭ ከሆኑ የግል ገጠመኞች ዙርያ ማውጋቱ የበለጠ ጉልህ ያደርገዋልና አንባቢዎቼም የራሳችሁ ገጠመኝ ዙርያ እየተሽከረከራችሁ የእኔን እንድትካፈሉ እጋብዛለሁ። በዚህ መልኩ ከምን ተነስተን የት እንዳለን ይታየናል።

እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በ 1966 ዓ ም ባህርዳር አፄ ሰርፀ ድንግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዘጠነኛ ክፍል አንድ ጠረጴዛ ተጋርቼ ከሁለት የኤርትራ ክፍለ ሃገር ተወላጆች ጋር ተቀምጫለሁ። በተለይ አንደኛው ባህርዳር ተወልዶ ያደገ የብቸኛው የከታማው ትልቁ ፋርማሲ ባለቤት የአቶ ማሞ ልጅ ነው። ሁለተኛው ጓደኛችን አስመራ ቢወለድም እድገቱ ባህርዳር ነው። አስራ አራቱንም ጠቅላይ ግዛቶች የያዘች የኢትዮጵያ ካርታ ሽፋን ያለበት ደብተር ሁላችንም ነበረንና የሁለታቸውም ደብተር ላይ የኤርትራን ካርታ በከለር አድምቀውበት "አደይ ኤርትራ" እያሉ እኔ ጓደኞቸውም እንዳይ እያደረጉ ወደ ልባቸው እያስጠጉ ያቅፉና ካርታውን ይስማሉ። ባግራሞት ስመለከታቸው ይውጣልህ ብለው ይመስላል "የአንተ አገር የቱ ነው?" ብለው ጠየቁኝ። ሙሉ የኢትዮጵያ ካርታን ሳመለክታቸው እየሳቁ "ኖ ኖ ኖ የተወለድህበትን ነው የምንጠይቅህ" አሉ፤ ከአካባቢው የመጣሁ የድሃ ገበሬ ልጅ መሆኔ ባይጠፋቸውም።

ባህርዳር ዕድሷ ሆኖ እንደሆነ አላውቅም ሰሞኑን ጎብኝቷት የመጣ ጓደኛዬ እንዳወጋኝ ከሆነ አሁን ደግሞ ትልልቆቹ ተቋማት ወዲህ ማዶ ባሉ ትግሬዎች ተይዘዋል። አንድ ውድ የግል ሆስፒታል ሊታከም ሄዶም ከተደረደሩት ተስተናጋጆች ሲቀላቀል ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል ትግርኛ ሲነገር ሰምቶ ትግራይ ያለ ያህል ተሰምቶትም ተመልሷል። የድሮዋ ባህርዳር ሁለተኛዋ አስመራ ትባል ነበር። በውበቷ ብቻ ሳይሆን በነዋሪዎቿም ጭምር እንጂ (የዛሬዋን ሁለተኛዋ መቀሌ ብለዋት ከሆነ አላውቅም)። ትልልቅ የኤኮኖሚ ተቋማት ባብዛኛው የተያዙት በኤርትራውያን ነበርና። በሌሎች ከተሞችም ጉልህ ቦታ ቢኖራቸውም የባህርዳሩ ሚዛን ከሌላው ጋር ሲነፃፀር ከፍ ይል ነበር። ጋራጆች፣ ሱቆች፣ ዳቦቤቶች፣ ሬስቶራንቶች፣ ዳንስቤቶች፣ የቢስኪሌት መሸጫና መጠገኛዎች፣ ዘይት መጭመቂያዎች ወዘተ. ሙሉ በሙሉ እስከሚባል ድረስ በኤርትራውያን ከመያዛቸውም በላይ በጥጥ ፋብሪካው፣ በመዘጋጃ ቤቱና በልዩ ልዩ መስሪያ ቤት ውስጥ ትልቅ ቦታ ነበራቸውና ትግርኛ ከአማርኛ ቀጥሎ የሚነገር በመሆኑ እኔም በሚገባ መነጋገር ጅምሬ ነበር። የምኖረው ኤርትራዊ በሆኑት አቶ አሰፋ አብርሃ ዶርም፣ የምመገበው እንደሁሉም የገጠር ልጆች አባ ነፀረ ቤት ልጆቻቸው መብራትና ተከስተ እያስተናገዱን፣ ብርሃነ፣ ጸጋ ዘአብ፣ ገብረሚካኤል( ኳስ ተጫዋቹ ጋራንቻ፣ ሻዕብያ ውስጥ ትልቅ ቦታ እንደነበረው ሰምቻለሁ)፣ ሃለፎም በሚባሉ መምህራን እየተማርሁ፣ አሜድላ ሻይ ቤት የበረከተአብና ሌሎችን ኤርትራውያን ሙዚቀኞች ዜማ እያዳመጥሁ፣ ሲርበኝ እነአባ አድጎ ዳቦ ቤት አሶድ(ጥቁር ርካሽ የስንዴ ዳቦ) እየገመጥሁ በትግርኛ ሳወራርደው ኖሬ ቋንቋውን ብሰማው የሚደንቅ አይሆንም። በትልልቆቹ የኤርትራውያን ሰርግ ከአስመራ የሚያስመጡአቸው አዝማሪዎች